የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 58
ADDIS ABABA - 22nd June, 1999

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶/፲፱፻፺፩ ዓ·ም·
የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........ ገጽ ፩ሺ ፷፬

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 50/1999
Educational Materials Production and Distribution Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations ........................................ Page 1064

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶/፲፱፻፺፩
### የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፡
"የትምህርት መሣሪያዎች" ማለት ለትምህርት መስጫ አገልግሎት የሚውሉ መጻሕፍት ፡ ሥዕላዊ መግለጫዎች ፤ ቻርቶች፡ ካርታዎች ፡ የሳይንስ ፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት መሣሪያዎች ፡ የትምህርት ተቋማት ቁሳቁሶች ፈርኒቸር ፤ የኦዶቪዥዋል መሣሪያዎች ፡ የሕፃናት መጫወቻዎች ፤ ልዩ ልዩ ፎርሞችና ሌሎችም ለትምህርት ዘርፍ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ናቸው ።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 50/1999.
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF EDUCATION MATERIALS PRODUCTION AND DISTRIBUTION ENTERPRISE

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia proclamation No. 4/1995 and Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Educational Materials Production and Distribution Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No.50/1999."

2. *Definition*

In these Regulations:
"Educational Materials" shall mean Textbooks, Visual Aids, Charts, Maps, Science and Vocational Instruments, Educational institutions furniture, Audio-visual instruments, Children's toys, different forms and other materials applicable in the education sphere.

Federal Negarit Gazeta — No. 58 22[nd] June, 1999—Page 1065

፫. መቋቋም

፩. የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ።

፬. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ።

፭. ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል ። እንደአስፈላጊነቱም በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ።

፮. ዓላማ

፩. የትምህርት መሣሪያዎችን ማምረት ፤ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ገዝቶ ማቅረብ ፤

፪. የሥልጠናና የሙያ ምክር አገልግሎት መስጠት ፤

፫. ትርፋማነትን ማሳደግና አስተማማኝ ገበያ መፍጠር ፤

፬. ዓላማዎችን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ ።

፯. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩፻፶ ሚሊዮን (አንድ መቶ ሃምሣ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህም ውስጥ ብር ፩፻፲ ሚሊዮን ፮፻፷፰ ሺ ፯፻፪ ብር ከ፸፬ ሣንቲም (አንድ መቶ አሥር ሚሊዮን ስድስት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ ሰባት መቶ ሁለት ብር ከሰባ አራት ሣንቲም) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፰. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ።

፱. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ።

፲. መብትና ግዴታ

ከአሁን ቀደም የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ይባል የነበረው ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፏል ።

፲፩. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Establishment*

1) There is hereby established a Public enterprise to be known as Educational Materials Production and Distribution Enterprise (Here-in-after called Enterprise)
2) The Enterprise shall be governed by the public Enterprise proclamation No. 25/1992.

4. *Supervising Authority*

A body to be designated by the Government shall be the Supervising Authority of the Enterprises.

5. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa. If necessary it may have branches elsewhere.

6. *Objectives*

Objectives of the Enterprise:

1) Production of educational Materials, Domestic and Foreign purchase;
2) To give training and professional consultancy service;
3) To increase profit and create stable market;
4) To engage in other related activities for the attainment of its objectives.

7. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise is 150,000,000 (One hundred fifty million Birr) of which 110,668,702.74 (One hundred ten million six hundred sixty eight thousand seven hundred two birr and seventy four cents) is paid in cash and in kind.

8. *Liability*

The Enterprise shall not be held liable beyond its total assets.

9. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

10. *Rights and Duties*

The rights and duties of the former Educational Materials Production and Distribution Agency are hereby transferred to the Enterprise.

11. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 22[nd] day of June, 1999.

MELES ZENAWI
Prime Minister of the Federal
Democratic Republic of Ethiopia

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE